## <u>የክፍል አባልነት ማስታወቂያ</u>

**አል ኦትሮ ላዶ ማየርካስ፣ ጉዳይ ቁጥር 17-02366 (ኤስ.ዲ. ካል.)**

**እርስዎ፡ (1) ከጁላይ 16፣ 2019 በፊት ጥገኝነት ለመጠየቅ በUS-ሜክሲኮ ድንበር ላይ በሚገኘው የመሬት መግቢያ ወደብ በኩል ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመግባት ፈልገው የነበረ ሲሆንነገር ግን (2) በመግቢያ ወደብ በመለኪያ ምክንያት እርስዎ ወደቡን አልፈው ወደ አሜሪካ መግባት አልቻሉም ነበር። እስከ ጁላይ 16 ቀን 2019 ድረስ ወይም ከዚያ በኋላ ወደ አሜሪካ ለመግባት አልቻሉም ነበር ። (3) የሜክሲኮ ዜጋ አይደሉም; እና (4) አሁንም በዩናይትድ ስቴትስ ጥገኝነት ለመከታተል ይፈልጋሉ። እነዚን ካሟሉ እርስዎ በአል ኦትሮ ላዶ ክፍል የድርጊት ክስ ውስጥ የቅድመ ማዘዣ ክፍል አባል ነዎት። የክፍል አባል ከሆንክ የፍርድ ቤት ውሳኔ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት "ሦስተኛው" በመባል የሚታወቀው የጥገኝነት ብቁነትን የሚገድብ ህግ በእርስዎ ላይ እንዳይተገብር ይከለክላል። የዚህ ክፍል አባል ከሆንክ እና የዩኤስ መንግስት በጥገኝነት ጥያቄህ ላይ የሶስተኛ ሀገር የመተላለፊያ ህግን አስቀድሞ ተግባራዊ ካደረጉበክ፣ ጉዳይህ እንደገና እንዲከፈት ወይም እንደገና እንዲታይ ልትጠይቅ ትችላለህ።**

ይህ ማስታወቂያ ከጠበቃ የቀረበ ጥያቄ አይደለም እና ምንም አይነት ጥቅማጥቅሞችን አይፈጥርም።

## <u>የቅድሚያ ትእዛዝ ስለ ምንድን ነው?</u>

አል ኦትሮ ላዶ ክርክር ከማየርካስ ጋር እሚባለው በዩኤስ-ሜክሲኮ ድንበር ላይ በሚገኙ የመሬት ወደቦች ላይ የዩኤስ መንግስት የ "መለኪያ" አጠቃቀምን የሚመለከት ክስ ነው። ፍርድ ቤቱ በዚህ ክስ ውስጥ የዩኤስ መንግስት "PI ክፍል አባላት" በመባል የሚታወቁትን ግለሰቦች ላይ "የሦስተኛ ሀገር የመተላለፊያ ደንብ" በመባል የሚታወቀውን ደንብ የአሜሪካ መንግስት እንዳይተገበር የሚከለክል "ቅድመ ትእዛዝ" (PI) ሰጥቷል።; የ"PI ክፍል አባላት" በመባል የሚታወቁትን ግለሰቦች :

> በዩኤስ መንግስት የመለኪያ ፖሊሲ(Metering) ምክንያት ከጁላይ 16፣ 2019 በፊት በዩኤስ (የመግቢያ ወደብ) በቀጥታ የጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ ያልቻሉ እና የዩኤስ የጥገኝነት ሂደትን ለማግኘት መፈለጋቸውን የቀጠሉት ሁሉም የሜክሲኮ ዜጋ ያልሆኑ ጥገኝነት ጠያቂዎች ያካትታል።

ፍርድ ቤቱ ቀጥሎ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት : የዩኤስ መንግስት (1) የPI ክፍል አባላት ሊሆኑ የሚችሉትን እንዲለይ፣ (2) በDHS በጥበቃ ሥር ያሉ ወይም በአስተዳደራዊ የኢሚግሬሽን ሂደት ውስጥ ያሉ ተለይተው የታወቁ የPI ክፍል አባላትን በPI ማስታወቂያ እንዲያቀርብ እና (3) በሦስተኛ ሀገር የመጓጓዣ ህግ ምክንያት የPI ክፍል አባላት እያሉ የጥገኝነት ጥያቂያቸው ውድቅ የሆነባቸው ግለሰቦች ጉዳያቸው ድጋሚ እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቷል። በእነዚህ የፍርድ ቤት ትዕዛዞች መሰረት፣ የPI ክፍል አባል ከሆንክ የአሜሪካ መንግስት የሶስተኛ ሀገር የመተላለፊያ ህግን በጥገኝነት ጥያቄህ ላይ ሊተገበር አይችልም። የ PI ክፍል አባል ከሆንክ እና መንግስት

በጥገኝነት ጥያቄህ ላይ የሶስተኛ ሀገር ትራንዚት ህግን ተግባራዊ ካደረገብክ ጉዳይህ እንደገና እንዲከፈት ወይም እንደገና እንዲታይ ልትጠይቅ ትችላለህ።

## "መለኪያ" ምንድን ነው?

የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት በዩናይትድ ስቴትስ እና በሜክሲኮ ድንበር ላይ ሰነዶች ያላሟሉትን እና ዜጋ ያልሆኑት ለመቆጣጠር መለኪያ ይጠቀማል።. የሚከተለው ከሆነ "መለካት" ተተግብሮብህ ሊሆን ይችላል፡-

– በዩኤስ-ሜክሲኮ ድንበር ላይ ወደሚገኘው የመሬት መግቢያ ወደብ ቀርበህ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመግባት መጠበቅ እንዳለብህ ወይም ወደቡ እንደተጨናነቀ እና አንተን ለማስኬድ አቅም እንደሌለው ከተነገረህ፤ ወይም

– በዩናይትድ ስቴትስ-ሜክሲኮ ድንበር አቅራቢያ ያለ የድንበር ከተማ ከደረስክ በኋላ በሜክሲኮ ውስጥ ስምህን በተጠባባቂዎች ዝርዝር ውስጥ ካስመዘገብክ (ወይም ይህን ለማድረግ ከሞከርክ)።

## "የሶስተኛ ሀገር የመጓጓዣ ህግ" ምንድን ነው?

የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት በጁላይ 16፣ 2019 "የሶስተኛ አገር የመተላለፊያ ደንብ" ተግባራዊ አድርጓል። "የሶስተኛ አገር የመተላለፊያ ህግ" አንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ከሌሉ አንድ ሰው ጥገኝነት ማግኘት እንደማይችል ገልጿል።

በዚህ ህግ መሰረት ኣንድ ግለሰብ (1) የሜክሲኮ ዜጋ ካልሆነ (2) ሜክሲኮ ላይ ወይም ሌላ ሃገር ላይ የጥገኝነት ወይም የከለላ ጥያቄ ካላቀረበ (3) ወደ ኣሜሪካ በዩኤስ ኣሜሪካ ሜክሲኮ ደንበር በኩል በጁላይ 16፣ 2019 በፊት ወይም በኋላ ከገባ የጥገኝነት ጥያቄው ውድቅ ይሆናል ይላል።

## ለምንድነው ይህን ማስታወቂያ የምቀበለው፣ እና ቀጥሎ ምን ይሆናል?

ይህ ማስታወቂያ የተቀበሉት የዩኤስ መንግስት መዛግብት የሚከተለውን ስለሚያመለክቱ ነው፡ (1) የ P1 ክፍል አባል ሊሆኑ ይችላሉ፤ (2) የዩኤስ መንግስት በእርስዎ የኢሚግሬሽን ጉዳይ ላይ "የሶስተኛ አገር የመተላለፊያ ደንብ" ተግባራዊ አድርጓል። (3) በ"የተፋጠነ የማስወገድ ትእዛዝ" ከዩኤስ እንዲወገዱ ታዝዘዋል። እና (4) በአሁኑ ጊዜ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እየኖሩ ይገኛሉ።

**ይህ ማስታወቂያ ከደረሰዎት እና አሁንም ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እየኖሩ ከሆኑ፣ የዩኤስ ዜግነት እና የስደተኞች አገልግሎቶች (USCIS) መስርያ ቤት በአካል የP1 ክፍል አባልነት ማጣሪያ ቃለመጠይቅ ያካሂዳሉ (ይህን የመሰለ ማጣሪያ ካሁን በፊት ካልተቀበሉ በስተቀር)። የUSCIS ጥገኝነት መኮንን ፊት ለማጣርያ ቃለመጠይቅ እንዲቀርቡ የሚጠይቅ የቃለ መጠይቅ ጥያቄ ወረቀት ከዚህ**

**ማስታወቂያ ጋር ተያይዞ ቀርቦሎትዋል ። በዚህ ሰዓት ዩናይትድ ስቴትስን ለቀው ከሄዱ ግን አሁንም በአሜሪካ ጥገኝነት መከታተል ከፈለጉ እና የዩኤስ መንግስት የሶስተኛ ሀገር የሙተላለፊያ ህግን በኢሚግሬሽን ጉዳይዎ ላይ ተግባራዊ አድርጓል ብለው ስለሚያምኑ PI ክፍል አባልነት ምርመራ መቅረብ ከፈለጉ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት: (1) የPI ክፍል አማካሪን በ [MeteringClass@splcenter.org](mailto:MeteringClass@splcenter.org). ያግኙ። እና (2) በተያያዘው የቃለ መጠይቅ ማስታወቂያ ላይ ከተዘረዘረው የጥገኝነት ቢሮ ጋር የአድራሻ/የዕውቂያ መረጃዎን ያዘምኑ።**

**ማሳሰብያ - ይህ ማስታወቂያ የPI ክፍል አባልነት ውሳኔ አይደለም።**

በምርመራው ወቅት የጥገኝነት ሹሙ ከጁላይ 16 ቀን 2019 በፊት ለመለካት ተገዢ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል። እንዲሁም በቃለ መጠይቁ መመሪያዎ መሰረት የPI ክፍል አባልነት ማረጋገጫ ማስረጃዎችን ለጥገኝነት ኦፊሰሩ ማቅረብ ይችላሉ። ማስረጃዎቹ እሚከተሉትን እና ሌሎች ነገሮችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ወደ ሜክሲኮ የተጓዙበትን እና የቆዩበትን ቀን የሚያሳዩ ሰነዶች፣ ስምዎን በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ገብቶ እንደነበር እሚያሳይ፣ እና ከጁላይ 16, 2019 በፊት “መለኪያ” ተተግብሮብዎት እንደሆነ እሚያሳይ መግለጫዎች ወይም ማረጋገጫዎች ሰነዶችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ያልተገደቡ አይደሉም። .

ዩ.ኤስ.ሲ.አይ.ኤስ (USCIC) እርስዎ የPI ክፍል አባል ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ ካመነ ለአዲስ ተአማኒነት ያለው ፍርሃት ቃለ መጠይቅ ቀጠሮ ይይዝሎታል።

**<u>እኔ PI ክፍል አባል ነኝ?</u>**

| ☑እርስዎ ከሚከተሉት የ PI ክፍል አባል ነዎት: | ✖ እርስዎ ከሚከተሉት የPI ክፍል አባል አይደሉም |
|---|---|
| ☑ የሜክሲኮ ዜጋ አይደሉም; ☑ ከጁላይ 16፣ 2019 በፊት "መለኪያ" ተተግብሮቦታል፤ | ✖ የሜክሲኮ ዜጋ ወይም ዜጋ ናቸው; |
| ☑ በ ጁላይ 16፣ 2019 ከዛ በፊት ወይም በኋላ ወደ አሜሪካ ለመግባት የዩኤስ-ሜክሲኮን ድንበር አላቋረጡም። | ✖ ከጁላይ 16፣ 2019 በፊት በአካል በUS ሜክሲኮ ድንበር ላይ ወይም አጠገብ አልነበሩም። |
| እና | ✖ በቅርቡ ከጁላይ 16፣ 2019 በፊት ወደ አሜሪካ ገብተዋል ወይም |
| ☑ ጥገኝነት ጠይቀዋል ወይም ፍርሃትን አለኝ ብለዋል እና አሁንም በ U.S ጥገኝነት መጠየቅ ይፈልጋሉ። | ✖ ቀደም ሲል በ U.S ጥገኝነት ተሰጥቶዎታል። |

ተጨማሪ መረጃ እንዴት አገኛለሁ?

ስለ እርስዎ የ PI ክፍል አባልነት ማጣሪያ ቃለ መጠይቅ ልዩ ጥያቄዎች ካሉዎት የኢሚግሬሽን ጠበቃዎን ወይም በተያይዘው የቃለ መጠይቅ ማስታወቂያ ውስጥ የተዘረዘረውን የጥገኝነት ቢሮ ማነጋገር ይችላሉ።

ስለ Al Otro Lado ክስ እና የቅድሚያ ትዕዛዝ ሌላ መረጃ በ MeteringClass@splcenter.org. ኢሜል በመላክ የPI ክፍል አባላትን (የክፍል አማካሪ) የሚወክሉትን ጠበቆች ማግኘት ይችላሉ። የክፍል አማካሪዎች የግለሰብ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ጉዳይ በመንግስት ፊት ሊወክሉ ኣይችሉም። ለመንግስት ተጨማሪ ወጪ እስካላስወጣ ድረስ የመረጡትን የተለየ የህግ ተወካይ ጠበቃ የማነጋገር መብት አልዎት።

ጥያቄዎች? ስለ እርስዎ የ PI ክፍል አባልነት ማጣሪያ ጥያቄዎች፣ በተያያዘው የቃለ መጠይቅ ማስታወቂያ ውስጥ የተዘረዘረውን የጥገኝነት ቢሮ ያነጋግሩ። ከአል ኦትሮ ላዶ v. ማዮርካስ ጋር ለተያያዙ ሌሎች ጥያቄዎች፣ የክፍል አማካሪን በ MeteringClass@splcenter.org. ኢሜል መላክ ይችላሉ።